በሕብረት በእምነት መጠንከር

viva
together for children

WORLD WEEKEND OF PRAYER
4 - 5 JUNE 2022

ዓለም ዓቀፍ የጸሎት ሳምንት
ግንቦት27 – 28 /2014 ዓ.ም
SHARON — Ethiopia
ሻሮን ኢትዮጵያ

የጸሎት ምንጭ

በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ (ሐዋ 2:46)

የዚህ ዓመት የዓለም ፀሎት ቀን ከጴንጤቆስጤ ቀን ጋር ተገጣጥሟል፡፡ ከፋሲካ ሀምሳ ቀናት በኋላ መንፈስ ቅዱስ የወረደበትን ቀን እናከብራለን፡፡ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ስናስብ በዘመኑ ለነበሩት ለኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ብቻ ሳይሆን አሁን ላሉት እና ወደፊትም ለሚኖሩት አማኞች ሁሉ እንደሆነ ልናስብ ይገባል፡፡ **ይህ ታላቅ ስጦታ፣ ዛሬም በኛ ዘመን በአብሮነት ውስጥ ኃይልን ሊሰጠን ከእኛ ጋር አለ፡፡**

የኮቪድ ወረርሽኝ ስርጭት ሁላችንንም አናውጦናል፡፡ አሁንም ዓለምን እያናወጠ ይገኛል፡፡ በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ እያደርሰ ያለው ቀውስ እና ሀዘን ቅስም ሰባሪ ሆኖ ቀጥሏል፡፡

ልጆችን ማዕከል ያደረገው የዚህ ዓመት የዓለም የፀሎት ሳምንት እንዴት ነው ያለንን እምነት እና ህብረት ሊያጠናክር የሚችለው? በጋራ የተጋረጠብንን ተጋላጭነት ልጆች እየመሩን በፀሎት እና በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት ውስጥ ባለው መታደስ እንጋፈጠው፡፡

በፍርሀት እና ስጋት ውስጥ ሆነው በመጀመሪያው **የጴንጤቆስጤ** ቀን በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉት 120 የሚሆኑ ጥቂት አማኞች የምንማረው ነገር አለ፡፡ ይሄውም በአስጊ ሁኔታ ውስጥ ሳሉ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸው ነገሮችን ሁሉ እንደቀየረ ነው፡፡ አነኚህ በፍርሀት ውስጥ የነበሩ ጥቂት የክርስቶስ ተከታዮች

'Pentecost' by Natacha Verny

እንዴት ነው ቁጥራቸው በአንድ ቀን ብቻ ወደ 3120 ያደገው? እንዴት ነው የእግዚአብሔር መንግስት በየቀኑ ያድግ የነበረው እና ጉድለት የነበረባቸውን "ስማናቸውም እንደሚያስፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉ የነበረው? (ሐዋ 4:35)?" መልሱ

መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

ይህንን የዓለም የፀሎት ሳምንት ምክንያት በማድረግ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተን እና በእምነታችን ጠንክረን በተሰበረ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩትን ልጆች ታዕምራዊ በሆነ ሁኔታ እንታደግ፡፡

ስለ ጴንጤቆስጤ ቀን አንድ አንድ እይታዎች

በሐዋርያ ስራ ምዕራፍ ሁለት በተለይ ከቁጥር 1-13 እና ከቁጥር 36-47 ስንመለከት በጴንጤቆስጤ ቀን የነበረውን ታሪክ በሚመለከት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን 12 አይታዎች እናገኛለን፡፡ እነኚህ እይታዎች በኮቪድ እና በሌሎች ችግሮች ምክንያት እንደማህበረሰብ የገጠሙንን ተግዳሮቶች እንዴት በእምነት በጋራ ማለፍ እንደምንችል ያስተምሩናል፡፡ ከአስራሁለቱ ውስጥ ያላችሁበተን ሁኔታ ሊገልፁ የሚችሉትን 4 ወይንም 5 እይታዎች ምረጡ፡፡

1. በስጋት ውስጥ መኖር

የኢየሱስ ተከታዮች እና ደቀመዛሙርት በእየሩሳሌም ከነበሩ የሀይማኖት መሪዎች የሚደርስባቸውን ስደት እና ዛቻ ሰምተው በመፍራት ውስጥ ነበሩ፡፡ በመሆኑም እርስ በእርሳቸው መደጋገፍ(መበረታታት) ነበራቸው፡፡ አሁን በእኛ ጊዜም ልጆች፣ቤተሰብ እና ማህበረሰብም ልክ እንደ ደቀመዛሙርቱ በከባድ ሁኔታ እና ተፅዕኖ ውስጥ እያለፉ ይገኛል፡፡

እስኪ ልጆች እና ወጣቶችን ምን እንደሚያስፈራቸው ጠይቋቸው፡፡

2. በጋራ መፀለይ

በሐዋርያ ስራ 1:14 ላይ የኢየሱስ ተከታዮች ሁልጊዜ በፀሎት አብረው ይተጉ ነበር፡፡ እኛም በዓለም ዙሪያ ካሉን አጋሮቻችን ጋር በመሆን እና በልጆች መሪነት ማድረግ የምንፈለገው ይሄንኑ ነው፡፡

በምን ጉዳይ ላይ ልንጸልይ እንደሚገባን ልጆችን እና ወጣቶችን ጠይቋቸው

3. እርስ በእርሳችን መበረታታት

በአካልም ይሁን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለጸሎት አንድ ላይ መሰብሰባችን ትልቅ ኃይል አለው፡፡ ስንገናኝ ልክ የኢየሱስ ክርስቶስ ወዳጆች እንዳደረጉት እርስ በእርሳችን መበረታታት እንችላለን፡፡

ልጆች እና ወጣቶች አጠገባቸው ላለው ሰው የሚያበረታታ ቃል እንዲናገሩ እርዷቸው

4. ጌታን መጠበቅ

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን "ከኢየሩሳሌም እንዳትወጡ" በማለት እንዲጠብቁ አዘዛቸው (ሐዋ 1:4) እነርሱም ታዘዙ፡፡

መታዘዝ እና ጌታን መጠበቅ በዚህ የፀሎት ሳምንት ልናስተጋባው የሚገባ መልካም መንፈሳዊ ዲሲፕሊን ነው፡፡ ተግባራትን ማከናወን ጥሩ ቢሆንም ከመውጣታችን በፊት በጌታ ፊት ቁጭ ብሎ መስማት ደግሞ የሚበልጥ ነገር ነው፡፡ ጌታ እግዚአብሔር ስለሚዋጋላችሁ ከእናንተ የሚፈለገው በፀጥታ መቀመጥ ነው (ዘፀ 14:4)፡፡

በፀጥታ ጌታን መጠበቅ መልካም የሚሆነው መቼ ነው

5. ኢየሱስ የሰጠውን ተስፋ ማስታወስ

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወዳቸው ለልጆች ማስታወስ መልካም ነው፡፡ እንደሚጠብቃቸው እና እንደሚንከባከባቸው ቃል ገብቶላቸዋልና፡፡ ደቀመዛሙርቱም የኢየሱስን ተስፋ ማስታወስ ነበረባቸው፡፡ "ከጥቂት ቀናት በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ" (ሐዋ ሥራ 1፤5)

ኢየሱስ የሰጣቸውን ተስፋዎች ዝርዝሩ

6. በመንፈስ መቀባት

በጴንጤቆስጤ ጊዜ በመጀመሪያ የንፋስ ድምፅ የሚመስል ድምፅ ነበር፡፡ "ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ንፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፡፡ ከዚያም እንደእሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው፡፡" ሰዎች በህበረት ሆነው ሲጸልዩ በመንፈስ ቅዱ የተሞሉበት በርካታ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ስለዚህ ስለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከልጆች ጋር ሆነን ስንጸልይ በግልጽ በመናገር እና በመጠባበቅ መሆን አለበት፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ልጆች ስለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ ያላቸውን ልምምድ ያካፍሉ፡፡

7. የእምነት እርምጃ

የጴንጤቆስጤ ውጤት ምንድን ነው? እነዚህ የሚፈሩ የኢየሱስ ጥቂት ተከታዮች እንዴት በቅፅበት ተለወጡ? በአስደናቂ ኃይል ተሞልተው በሁሉም ቋንቋዎች ተናገሩ፡፡ ያ ነው ለእኛም በዚህ ዘመን የሚያስፈልገን እና ለእኛም የተሰጠ ነው፡፡ "መንፈስ ቅዱስም ይናገሩ ዘንድ አቅም ሰጣቸው፡፡" (ሐዋ ሥራ 2:4)

እኛ ወጣቶች በማህበረሰብ ውስጥ ምን መስራት እንችላለን

8. ተጠራጣሪዎች እና ተቀዋሚዎች

ተቃዋሚዎች ሁሌም አሉ፡፡ ምንም እንኳን ለሰዎች እና ለምንኖርበት ማህበረሰብ መልካም ነገር ብናደርግም ተቃዎሞ አይቀርም፡፡ በሐዋ 2:13 ላይ ለምሳሌ የኢየሱስ ተከታዮች በመንፈስ ሲፀልዩ ብዙዎች ባለማመናቸው ምክንያት ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥተዋል ብለው አፈዙባቸው፡፡

ምን አልባት ወደ ቤተክርስቲያን በመሄዳችሁ ወይንም ወደዚህ የጸሎት ሳምንት ስብሰባ በመምጣታችሁ ምክንያት ሰዎች አሹፈዎባችሁ ይሆን?

9. የመፍስ ቅዱስ ስራ ውጤት - የ3000 አማኞች መጨመር

እነዚህ ሁሉ ተቃዎሞዎች እና መሰናክሎች ቢኖሩም እንኳን መንፈስ ቅዱስ እንዴት ድፍረት እንደሞላባቸው እና 3000 አዳዲስ አማኞች እንደተጨመሩ ስናስብ ያስገርማል፡፡ በዚህ የዓለም የፀሎት ሳምንት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የልጆቻችንን እና የወጣቶችን ህይወት በመቀየር የወሰኑ ሌሎች ሦስትሺዎችን ሊያመጣልን እንደሚችል እንመን!

በዚህ የዓለም የጸሎት ሳምንት ልናልመው የምንችለው ትልቅ ህልም ምንድነው?

10. ለተቸገሩ ሁሉ ማካፈል

በደቀመዛሙርቱ ህይወት ዘውትር ከመገናኘት እና ከንግግር ያለፈ ተግባርም ነበራቸው፡፡ ያላቸውን ሁሉ እሸጡ ለሌላቸው ያካፍሉ ነበር ሐዋ 2:45፡፡ እኛም ችሮች እና ለጋሶች እንሁን!

እኛ ልጆች እና ወጣቶች የተቸገሩ ሰዎችን ህይወት ለመለወጥ በህብረት ምን ልናደርግ እንችላለን?

11. እግዚብሔርን በአንድነት ማመስገን

በዚህ በዓለም የፀሎት ሳምንት እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲሰራው የሚችለውን ስናስብ አምላካችንን በህብረት ማመስገንንም መዘንጋት የለብንም፡፡ ብዙ ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ ልመናዎቻችንን በጌታ ፊት ለማቅረብ በህብረት ስንሰበሰብ እንታያለን ነገር ግን ለማመስገን በህብረት መሆንን ብዙ ጊዜ አናስበውም፡፡ በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቁረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር ሐዋ 2:46

እኛ ልጆች እና ወጣቶች እግዚአብሔር በህይወታችን እንዲሰራቸው ስለምንጠብቃቸው ታላላቅ ነገሮች ጌታን ለማመስገን መቼ ነው እንደገና የምንሰባሰበው?

12. የእግዚአብሔር እለት እለት መስፋት

እስቲ በጴንጤቆስጤ ቀን የሆኑትን ነገሮች በህይወታችን እንግለጠው፡፡ ቀጣይነት ያለው እና እውነተኛ የሆነ በእምነት መነቃቀትን እና ማህበራዊ ደህንነትን አጥብቀን እንፈልግ፡፡ ከዚያም በየእለቱ ለውጥ እና መቀጣጠል እንመለከታለን ልክ በጴንጤቆስጤ ቀን እንደሆነው ማለት ነው፡፡ በህብረት በእምነት መጠንከርን በምናስብበት በዚህ ቀን ይህ በህይወታችን ሲሆን እንደሚችል እንመን!

ልጆችን እና ወጣቶችን፡- ተጨማሪ ልጆችን እንዴት አድርገን የዚህ አካል ማድረግ የምንችልባቸውን መንገዶች እንዲነግሩን እንጠይቃቸው፡፡

ልጆችን የሚያሳትፉ ተግባራት (Activity ideas)

የሚነጥቅ አውሎነፋስ

እያንዳንዱ ልጅ ባዶ የስስላሳ ጠርሙስ/ሀይላንድ የሚያስፈስገው ሲሆን ባስ ጠባብ አንገት ያለው ቢሆን ይመረጣል፡፡ ተራርቆ በመቀመጥ ክብ ሰርተው በጸጥታ ይቀመጡ፡፡ ቁጭ ብለው ይጠብቁ፡፡ ከዚያ ተራ በተራ ከጠርሙሱ ድምጽ እንዲያወጣ በአፋቸው እፍ ማለት ይጀምሩ፤ ልክ እንደ ኃይለኛ የንፋስ ድምፅ እስኪመስል ድረስ እፍ ይበሉት፡፡ ከዛ ግማሾቹ ጠርሙሳቸውን ውሀ በመሙላት የተለያዩ ድምፃችን ለማውጣት ይሞክሩ፡፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ቆንጆ መዝሙር ካላችሁ የመጀመሪያዎቹን ጥቂት ኖቶች ለመደጋገም ሞክሩ፡፡ ለብዙሀኑ ለማድረስ ሲባል በሚመች የጊቢ በር ላይ በመሆን ደጋግሙት፡፡ (የኮቪድ ህጎችን ማክበራችሁን ሳትረሱ ማለት ነው)

የዕሳት ነበልባል እና የመናገር ኃይል



የእሳት ነበልባልን የሚወክሉ ቀይ ቁርጥራጭ ጨርቆችን ያዘጋጁ፡፡ በእነዚህ ቀይ ቁርጥራጭ ጨርቆች በእንጨት ጫፍ ላይ በማሰር ባንዲራ ይስሩ፡፡ ወይም ደግሞ በቀይ ቀለም በረጅሙ የተሰመረ ወረቀት ይስሩ፡፡ ልጆቹ ክብ ሰርተው ተራርቀው ይቀመጡ፡፡ ከዛ በኋላ በክቡ ዙሪያ በመዞር ባንዲራውን በማውለብለብ በመረጠው ልጅ ላይ የእሳቱን ነበልባል/ባዲራውን ያስቀምጥበት(ይጣልበት)፡፡ ባንዲራው የተቀመጠበት ልጅ "እግዚአብሔር ይክበር" እያለ ይናገር፡፡ "እግዚአብሔር ይመስገን" የሚለውን በተለያየ ቋንቋዎች እንዲናገሩ ለማድረግ ሞክሩ፡፡ ይህንን ለማድረግ ግን ቀድማችሁ በልጆች ቁጥር ልክ ቋንቋዎችን በመምረጥ እና "እግዚአብሔር ይክበር" የሚል ፅሁፍ ያለበት ካርድ በማዘጋጀት ማለማመድ ያስፈልጋል፡፡

ባንዲራው የተጣለበት ልጅ አግዚአብሔር ይመስገን/የክበር ካለ በኋላ ይነሳ እና ባንዲራውን ይዞ በመዞር እርሱም በመረጠው ልጅ ላይ ያስቀምጣል፡፡ ሁሉም ልጆች አስኪደርሳቸው ድረስ ደጋግሙት እና ሁሉም ከደረሳቸው አንድ ላይ እግዚአብሔር ይመስገን ይላሉ (ሁሉም በተለማመዱት ቋንቋ)፡፡

ሦስት ሺህ ተጨመሩ

አንድ ትልቅ ልሙጥ ወረቀት አዘጋጅ (ለምሳሌ 4 ልሙጥ ወረቀቶችን አንድ ላይ በማጣበቅ ተለቅ ያለ ወረቀት መፍጠር ትችላላችሁ - አጠቃላይ መጠኑ 2.5 ሜትር x 3.7 ሜትር)፡፡ አሮጌ ማሸጊያ ወረቀት ላይም መስራት ይቻላል፤እላዩ ላይ ስዕል ለመስራት እስከተቻለ ድረስ ማለት ነው፡፡

ልጆች እና ወጣቶች አንድ ቡድን በመሆን የሚኖሩበትን አከባቢ ካርታ ወረቀቱ ላይ እንዲስሉ አድረጓቸው፡፡

እንደባልዲ ወይንም ኩባያ አይነት ያሉ ማከማቻዎችም ያስፈልጋሉ፡፡ ከዛ ውጡ እና ትንንሽ ድንጋዮችን ሰብስቡ፡፡ 13 ኩባያዎችን አዘጋጁ፡፡ እያንዳንዱ ኩባያ ወይንም ባልዲ 250 እስከ 250 የሚደርሱ ጠጠሮችን/ትናንሽ ድንጋዮች መያዝ አለበት፡፡

አንድ ኩባያ ላይ ከጴንጤቆስጤ ቀን በፊት የሚል ምልክት/ጽሁፍ ጻፉበት፡፡ ሁለት ልጆች ለዚህ ኩባያ/ባልዲ 120 የሚደርሱ ጠጠሮችን በመቁጠር ይጨምሩ፡፡ በካርታው ላይ ቤ/ክ ወይንም መሰብሰቢያ ቦታ የሚል ካለ ይህንን ባልዲ እዚያጋ ያስቀምጡ (የሳሉት ካርታ ላይ ማለት ነው)፡፡

ከዛ በመቀጠል ሌሎቹን 12 ባልዲዎች ከጴንጤቆስጤ ቀን በኋላ የሚል ጽሁፍ/ምልክት አድርጉባቸው፡፡ በጋራ በመሆን እያንዳንዱን መያዣ ውስጥ 250 ጠጠሮች ይሙሏቸው፤በ12 ኩባያዎች ውስጥ በጥቅሉ (በድምሩ) ስንት (ምን ያህል)ጠጠሮች ይገኛሉ?3000፡፡
ቀጥሎ የጸሎት ጊዜ ይሆናል፡፡ ልክ እንደጴንጤቆስጤ ቀን ኢየሱስ የልጆችን እና የወጣቶችን ህይወት ለመቀየር የሚሰሩ አገልጋዮችን (ልጆች እና ወጣቶች) በሚኖሩበት አከባቢ 3000 እንዲሆኑ ጌታን ጠይቁት፡፡ እያንዳንዱ ልጅ የመፀለይ እድል ከደረሰው በኋላ በ12ቱ ኩባያዎች ያሉትን ጠጠሮች በካርታው ላይ በትኗቸው፡፡ አሁን ጌታ ልምናችሁን ሰምቶ በምትኖሩበት አከባቢ የሚኖሩትን ልጆች እና ወጣቶች ህይወት ለመቀየር ስለሚሰራው ድንቅ ነገር አመስግኑት፡፡

ምስክርነቶች ከ2021

ህንድ

በህንድ ሀገር በአሻ ፎረም ባንግሎር በሚባል ቦታ ተስፋው የታደሰው የ12 አመት ልጅ ነው፡፡ ቀድሞውኑ በቤተሰቦቹ ተነግሮት የነበረው ሙሉ ሰፈሩ በኮቪድ ሲጠፋ እንደሚችል በመሆኑ

ፈርቶ ነበር፡፡ ቢዚህም ምክንያት ወደ ውጪ መውጣት እጅግ ፈርቶ ያስቀስ ነበር፡፡ ከዚያም ለልጆች መማለድ እና መፀለይ ጀመረ፡፡ በተለይ ደግሞ ክትባቱ በእነሱ አካባቢ እንዲገኝ ፀለየ፤ ከዛ በሁለት ሳምንት ውስጥ መንግስት በእነሱ ሰፈር ውስጥ ባለው ክሊኒክ ውስጥ ክትባቱን መስጠት ጀመረ፡፡

ካምቦዲያ

በካምቦድያ ፀሎት እንድትመራ የተደረገች አንዲት ሴት ልጅ ጸሎት እንድትመራ ስለተፈቀደላት ትልልቆች እንደሚቀበሏት እና እንደሚያከብሯት እንደተሰማት መስክራለች፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ሌላ ልጅ ቤተክርስቲያኗ ለልጆች ለመጸለይ ልዩ ቀን መዘጋጀቱ የመወደድ እና የመከበር ስሜት እንዲሰማት እንዳደረጋት መስክራለችች፡

የፀሎት ርዕሶች ከዓለም ዙሪያ

የአለም ካርታ ፕሪንት ካደረጋችሁ በኋላ እያንዳንዱን ልጅ እና ወጣቶች ከሀገራቸው ውጭ ለየትኛው ሀገር በትኩረት መፀለይ እንደሚፈልጉ ይምረጡ፡፡

ስማርት ስልክ ካላችሁ እና የኢንተርኔት አክሰስ ካለ ደግሞ ስለ ከተማዋ ከኢንተርኔት ላይ አንድ አንድ መረጃዎችን ማየት፡፡ ከዛ ስለራሰቸው እና ስለዚህ ስለመረጡት ሀገር/ከተማ ይጸልዩ፡፡

የዚህ ጸሎት ዋና ሀሳብ/ቁም ነገር ሁለት ከተሞችን በፀሎት ማያያዝ ነው፡ በሕብረት በዕምነት መጠንከር የሚለውን ሀሳብም ያንጸባርቃል፡፡

ለመረጣችሁት ሀገረ/ከተማ በምን ርዕስ ልትጸልዩ እንደምትችሉ የሚከተሉት ታሪኮች ሀሳብ ሊሰጣችሁ ይችላሉ፡፡

- እናቴን፣ አባቴን ወይም አያቴን በኮቪድ ምክንያት አጥቻለው፡፡
- እናት እና አባቴ በኮቪድ ምክንያት ስራ እንዳቆሙ ነው እስከአሁን አልጀሩም፡፡
- በጦርነት ምክንያት ቤተሰቦቻቸውን ላጡ ለተፈናቀሉ ቤት ንብረታቸውን ከብቶቻቸውን ሁሉ በማጣት ለከፍተኛ ጉስቁልና ለተጋለጡ ኢትዮጵያውያን እንጸልይ
- በዋጋ ንረት ምክንያት የዕለት ኑሮአቸውን መደጎም አቅቶቸው ለጎዳና ተዳዳሪነት ለሚጋለጡ ሁሉ እንጸልይ
- በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ነው የምንበላው ምክንያቱም ምግብ የምንገዛበት ገንዘብ የለንም፡፡
- በኮቪድ ምክንያት ቤታችንን ለቀን በሌላ መንደር ውስጥ እየኖርን ነው፣ ወደቤታችን ገና አልተመለስንም ጓደኞቼም በጣም ናፍቀውኛል፡፡
- ለረጅም ጊዜ ትምህርት ቤት መሄድ አልቻልኩም፤አሁን ለመማር እየከበደኝ ነው፡፡
- ቤቴ ውስጥ ፀብ አለ በዚህም ምክንያት ከቤት ወጥቼ መንገድ ላይ ጎዳና ላይ እየተኛሁ ነው፡፡ ጎዳና ላይ መኖር ደግሞ እጅግ አደገኛ ነው፡፡
- እኛ ሰፈር እየመጡ ብዙ ገንዘብ ይሰጡ ሰዎች አሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉት ግን ወንጀሎችን እና ሌሎች መጥፎ ነገሮችን በልጆች ማሰራት ስለሚፈልጉ ነው፡፡
- እናቴ በኮቪድ ተይዛ ነበር፤እናም በጣም ታማ ነበር፤እስከአሁን አልተሸላትም፤ምክንያቱም ልትታከም እና መድሀኒት ልትገዛ የምትችልበት አቅም የላትም ምን ላደርግ እችላለሁ?

ቁጥራቸው ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ልጆች የሚከተለውን ጸሎት እንዲጸልዩ እናድርግ

ጊታ ሆይ ከተማችንን ለልጆች እና ለወጣቶች ምቹ ለፍራ እንዲሆኑ ማድረግ የምንችልበትን ጥንካሬ እና እምነት ስጠን፡፡

viva
together for children